# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የኮቪድ ኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) በአሁኑ ጊዜ ለ 4ኛ ዙር የኮቪድ ኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም (CRRP) ማመልከቻዎችን እየተቀበለ ነው። እባክዎትን በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ከዚህ ቀጥሎ መልስ ያግኙ። ተጨማሪ መረጃ እና የማመልከቻ ሊንክ በዚህ ድህረ-ገጽ ይገኛል፤ www.mc311.com/rentrelief

**የቤት ኪራይ ለመክፈል እየተቸገርኩ ነው። ድጋፍ ይኖራል?**

ከኮቪድ ጋር በተያያዘ የገንዘብ ችግር ምክንያት በኪራይ ክፍያዎ ወደ ኋላ ከቀሩ ፣ ድጋፍ ሊኖር ይችላል። እባክዎን እዚህ የሚገኘውን የኦላይን ማመልከቻ ይሙሉ። በኦንላይን ማመልከቻውን እራስዎ ወይም ከባለንብረቱ/ከአከራዩ ሰራተኛ በመታገዝ መሙላት ካልቻሉ፣ እባክዎን እርዳታ ለመጠየቅ 311 (240-777-0311) ይደውሉ። ማመልከቻውን አጠናቆ ለመሙላት የካውንቲ ሰራተኛ ወይም አጋር ድርጅት ይደውልልዎታል።

**እንዴት ነው ማመልከት የምችለው?**

በቀጥታበዚህ በኮቪድ የቤት ክራይ ድጋፍ ድህረ-ገጽ ላይ ማመልከት ይችላሉ፤ www.mc311.com/rentrelief ኮቪድ በቤተሰብዎ ላይ ስላሳደረው ተጽእኖ እና ስለቤተሰብዎ አባላት ፤ ገቢ እንዲሁም ኪራይ አንዳንድ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይጠየቃሉ። እባክዎን ደጋፊ ሰነዶችን ለመጫን እና የአከራይዎን መረጃ ለማቅረብ ዝግጁ ይሁኑ። ማመልከቻውን ለመሙላት የኢሜል አድራሻ እንደሚያስፈልግዎት እባክዎ ይገንዘቡ። የኢሜል አድራሻ ከሌልዎት፣ እባክዎን የኢሜል አድራሻ ያውጡ ወይም ባለንብረቱ/አከራይዎ ወይም ሌላ ሊያግዝዎ የሚችል ሰው ይፈልጉ።

**የኢንተርኔት አገልግሎት የለኝም፣ ማመልከቻውን ለመሙላት ከባለንብረቱ/አከራዬ እርዳታ ማግኘት አልችልም። እንዴት ነው ማመልከት የምችለው?**

ማመልከቻውን ለመሙላት የኢንተርኔት አገልግሎት ከሌልዎት ወይም ለማመልከት እገዛ ካስፈለገዎት የካውንቲው ተወካይ ወይም አጋር እንዲደውልልዎት ለመጠየቅ ወደ MC 311 (240-777-0311) ይደውሉ። MC311 መሰረታዊ መረጃዎችን ከእርስዎ ይወስዳል፣ በመቀጠል የፕሮግራሙ ተወካይ ማመልከቻውን ለማጠናቀቅ ሊረዳዎ ወደ እርስዎ ይደውልልዎታል።

**ማመልከቻዬን ለማስገባት ቀነ ገደብ አለ?**

አዎ፣ ፕሮግራሙ ማመልከቻ መቀበያው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ለ45 ቀናት ብቻ ማመልከቻዎችን ይቀበላል። እባክዎን ያስተውሉ፤ ከአካባቢው መካከለኛ ገቢ (AMI) 50 በመቶ ወይም ከዚያ ያነሰ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የሚመጡ ማመልከቻዎች ብቻ ለገንዘብ ድጋፉ ግምት ውስጥ ይገባሉ። ተጨማሪ ገቢ የሚያገኙ ቤተሰቦች ማመልከቻዎች ተቀባይነት የላቸውም በተጨማሪም፣ የገንዘብ ድጋፉ ውስን በጁንም30፣ም2022ምቢያንስምለሁለትምወራትምየኪራይምክፍያምግዴታቸውንምያልተወጡምወይምምያልከፈሉ።

**ለኮቪድ ኪራይ እገዛ 4ኛ ዙር ፕሮግራም ብቁ የሆነው ማነው?**

ቤተሰቦች ብትንሹ የሚከተሉትን የብቃት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። የቤተሰብ አባላት፥

- የገንዘብ ችግር ያጋጠማቸው ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዘ መሆን አለበት፣
- በ 2020/2021 ታክስ ወይም ላለፉት 30 ቀናት አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢዎ ከአካባቢው አማካኝ የገቢ መጠን 50 በመቶ ወይም ከዚህ በታች መሆን አለበት፣
- ቢያንስ ከኦገስት 2021 ጀምሮ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የኖሩ መሆን አለበት፣
- በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መንገድ የቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው እና
- ቢያንስ ለሁለት ወራት ያህል የኪራይ ግዴታቸውን መወጣት ያልቻሉ መሆን አለበት፣።

**የአሜሪካዊ ዜግነት መስፈርት ነው? በማመልከቻው ውስጥ የማህበራዊ ዋስትና (ሶሻል ሴኪዩሪቲ) ቁጥር ይጠየቃል?**
አይጠየቅም፣ ህጋዊ የመኖርያ ማስረጃ አይጠየቅም። የዚህ ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ በኮንግረስ የፀደቀው የኮሮና ቫይረስ ያስከተለውን ተጽኖ ለመቀነስ የወጣ የድጋፍ ህግ አካል ነው። ይህ የአደጋ ጊዜ እርዳታ ስለሆነ፣ የቤተሰብ ህጋዊ የመኖሪያ ማረጋገጫ ሰነድ አያስፈልግም። በተመሳሳይ የማህበራዊ ዋስትና (ሶሻል ሴኪዩሪቲ) ቁጥሮች አያስፈልጉም።

**የገንዘብ ችግር ሲባል ምን ማለት ነው?**
ከኮቪድ-19 ጋር የተገናኘ ወይም የተከሰተ የገንዘብ ችግር ብዙ መልክ ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ፣ ሥራ አጥተው ወይም የስራ ሰአትዎ ተቀንሶ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ልጆችዎን ለመንከባከብ፣ የታመሙ የቤተሰብ አባላትን ለመንከባከብ ወይም እራስዎ ሆስፒታል በመግባትዎ ምክኒያት ሥራ ለማቆም ተገደው ይሆናል። በማመልከቻው ውስጥ ኮቪድ-19 እርስዎ እና ቤተሰብዎ ላይ እንዴት ተጽኖ እዳሳደረ በትክክል ለማብራራት የሚያስችልዎ ክፍል አለ።

**AMI ምንድን ነው ? ገቢዬ ከ AMI 50 በመቶ በታች መሆኑን እንዴት አውቃለሁ?**
AMI ማለት የአካባቢው መካከለኛ የገቢ አማካኝ ማለት ነው። በአካባቢው የሚገኙ ሁሉም ቤተሰቦችን "መካከለኛ" ገቢን በማየት የሚሰላ ነው። ከታች ያለው ሠንጠረዥ ከፍተኛውን ዓመታዊ ወይም ወርሃዊ ጠቅላላ የገቢ መጠን ይዘረዝራል።

| ***Family Size*** | *Max. Monthly Gross Household Income* ***50% AMI*** | *Max. Yearly Gross Household Income* ***50% AMI*** |
|---|---|---|
| 1 | $4,154 | $49,850 |
| 2 | $4,746 | $56,950 |
| 3 | $5,338 | $64,050 |
| 4 | $5,929 | $71,150 |
| 5 | $6,404 | $76,850 |
| 6 | $6,879 | $82,550 |
| 7 | $7,354 | $88,250 |
| 8 | $7,829 | $93,950 |

**ምን ምን አይነት ገቢ ሪፖርት መደረግ አለበት እና ይህንን ለማሳየትስ ምን ማካተት አለብኝ?**
አመልካቾች የእያንዳንዱን የቤተሰባቸውን አባላት ትክክለኛ ቁጥር እና 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ከሙሉ ጊዜ ተማሪዎች በስተቀር የሁሉም የቤተሰብ አባላት ገቢ ማካተት አለባቸው።

የቤተሰብ ጠቅላላ ገቢ በ 2020 ወይም በ 2021 የታክስ ተመላሽ ላይ እንደሚታየው ወይም ባለፉት 30 ቀናት የተገኘ ጠቅላላ (ከታክስ በፊት ወይም ተቀናሾች) ገቢ ሪፖርት መደረግ አለበት። ሪፖርት የተደረገው ገቢ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እና ሌሎችንም ሊያካትት ይችላል ደሞዝ፣ ማህበራዊ ዋስትና (ሶሻል ሴኪዩሪቲ)፣ ጥቅማጥቅሞች ወይም ጡረታዎች፣ የመንግስት ድጋፍ፣ ስራ አጥነት፣ የወለድ ገቢ እና ወይም የልጅ ድጋፍ። ባለፉት 30 ቀናት የተገኘ ገቢ የስራ ክፍያ ፔይ ስታምፕ፣ የባንክ ስቴትመንት፣ የአሰሪ ደብዳቤዎችን ወይም በራስዎ የተረጋገጠ ማስረጃ በመጠቀም መመዝገብ ይቻላል።

**ከኦገስት 2021 ጀምሮ መልቀቅ ካለብኝ ፤ ለድጋፉ ብቁ እሆናለሁ?**

ይሆናሉ፤ አሁንም የተከራይ ሃላፊነት እስካለብዎት ድረስ እና ከኦገስት 2021ወይም ከዚያ በፊት የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ነዋሪ ከነበሩ። ምንም እንኳን ከዚያ ቀን በኋላ በካውንቲው ውስጥ አድራሻ ቢቀይሩም ፣ የኪራይ ሃላፊነት እስካለብዎት ድረስ አሁን ባሎት የሞንትጎመሪ ካውንቲ አድራሻ ለእርዳታ ማመልከት ይችላሉ።

**አንዳንድ የቤተሰብ ወጪዎችን ለመክፈል ከጓደኛ/የቤተሰብ አባል ጋር ስምምነት አለኝ ፣ ነገር ግን የራሴ የኪራይ ውል የለኝም። አሁንም ለእርዳታ ብቁ ነኝ?**

የቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ እስካለብዎ ድረስ መደበኛ ያልሆነ የሊዝ ውል ቢኖርዎትም ለድጋፍ ብቁ ነዎት። ለቤት ኪራይ ሊከፍሉት የተስማሙት ሰው በየወሩ ምን ያህል መክፈል እንዳለብዎ እና ምን ያህል እንደከፈሉ/እንደቀረብዎ በጽሁፍ ማረጋገጥ ይኖርበታል። <u>ነገር ግን፣ በውልደት ወይም በጋብቻ ከአከራይዎ ጋር የተዛመዱ ከሆኑ እና ግለሰቡ የቤቱ ባለቤት ከሆነ ኪራይ እንዲከፍሉ ልናግዝዎ አንችልም።</u>

**ከመኖሪያ ቤት ድጎማ ፕሮግራም (ሀውሲንግ ቾይስ ቫውቸር፣ የኪራይ እርዳታ ፕሮግራም ወዘተ) የቤት ኪራይ ለመክፈል እርዳታ እቀበላለሁ ፤ አሁንም ለማመልከት ብቁ ነኝ?**

አዎ። አሁንም ለማመልከት ብቁ ነዎት፣ ነገር ግን ድጋፍ ሊሰጥ የሚችለው የእርስዎ ሃላፊነት በሆነው የኪራይ መጠን ላይ ብቻ ነው። የኪራይ ሃላፊነትዎ እንዲስተካከል የእርስዎን የገቢ ለውጥ ለድጎማ ሰጪዎ እንዲያሳውቁ እጥብቀን እናበረታታዎታለን።

**ምን ያህል የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት እችላለሁ?**

ማመልከቻው በሚታይበት ጊዜ ባለው የድጋፍ የገንዘብ መጠን መሰረት፣ ከአካባቢው መካከለኛ ገቢ 30 በመቶ ወይም ከዚያ በታች የሚያገኙ ቤተሰቦችን አጠቃላይ የኪራይ ዕዳቸው ድረስ እና እስከ 2,000 ዶላር የሚደርስ በድምሩ የ18 ወራት የፍጆታ ዕዳን መክፈል ለሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ናቸው፣ ይህም ማንኛውንም የCRRP 3ኛ ዙር ድጋፍን ይጨምራል። ከአካባቢው መካከለኛ ገቢ 31 በመቶ እስከ 50 በመቶ ገቢ ከሚያገኙ ቤተሰቦች የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በድምሩ 12,000 ዶላር ወይም የ18 ወራት እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ (ከሁለቱ ያነሰውን) ፣ የCRRP 3ኛ ዙር ዕርዳታን ጨምሮ። የገንዘብ ድጋፉ ለኪራይ ክፍያ ብቻ ይውላል እና ከዚህ በፊት ከኮቪድ የቤት ኪራይ ድጋፍ ወይም ከሌሎች የአካባቢያዊ፣ የስቴት ወይም የፌደራል የገንዘብ ድጋፎች የተቀበሉትን የገንዘብ ድጋፎች ግምት ውስጥ ያስገቡ። ከ50 በመቶ በላይ አካባቢያዊ አማካኝ ገቢ (AMI) የሚያገኙ ቤተሰቦች ማመልከቻዎች ግምት ውስጥ አይገቡም።

**ቀደም ባሉት የ CRRP ዙሮች ውስጥ ድጋፍ አግኝቻለሁ፣ ግን አሁንም በኪራይ ክፍያ ወደ ኋላ ቀርቻለሁ። ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት እችላለሁ?**

አዎ። ቀደም ባሉት ዙሮች የኮቪድ ኪራይ ፕሮግራም ድጋፍ የተቀበሉ ቢሆንም እስከ ፕሮግራሙ የጊዜ ገደብ ድረስ ለተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ እንደገና ለማመልከት ይችላሉ። <u>ለአሁኑ ዙር (4ኛ) የገንዘብ ድጋፍ አስቀድመው ከተቀበሉ፤ እንደገና ማመልከት አይችሉም።</u>

**ማመልከቻዎች እንዴት ነው የሚስተናገዱት? ቅድሚያ የመጣ፤ ቅድሚያ ይስተናገዳል?**

አይደለም፣ ማመልከቻዎች ቅድሚያ የመጣ፤ ቅድሚያ ይስተናገዳል/ ድጋፍ ያገኛል በሚል መሰረት አይስተናገዱም። በመሆኑም፣ ማመልከቻዎች ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መስፈርት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ማመልከቻዎች ለግምገማ በሚመረጡበት ጊዜ፤ፕሮግራሙ ማንኛውንም ከቤት የማስወጣት የፍርድ ቤት ሂደቶች፤ የቤተሰብ ገቢ እና የመኖሪያ አካባቢ ግምት ውስጥ ያስገባል።

**ገንዘቡን በቀጥታ እቀበላለሁ?**

በአብዛኛው ግዜ፣ ድጋፉ በቀጥታ ለባለንብረቱ/አከራዩ የቤት ኪራይ ሂሳብዎን ለመክፈል ይላካል። ከአከራይዎ ጋር በቀጥታ መስራት ወይም መገናኘት ካልቻልን ክፍያው በቀጥታ ለእርስዎ ሊሰጥዎት ይችላል።

**ምን አይነት ሰነዶች ያስፈልጉኛል?**

ማመልከቻዎን ለመሙላት/ለማጠናቀቅ የሚከተሉት ሰነዶች ያስፈልገዎታል፣

- **የፎቶ** መታወቂያ፣ለእያንዳንዱ አዋቂ የቤተሰብ አባል የመንጃ ፍቃድ፣ ፓስፖርት ወይም ሌላ ይፋዊ የፎቶ መታወቂያ ኮፒ።
- **የመኖሪያ ቦታ/አድራሻ ማረጋገጫ** ፣ ለገንዘብ ድጋፍ በሚያመለክቱበት አድራሻ ሰለመኖርዎ የመኖሪያ ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል። ይህንን በባንክ ስቴትመንት፣ ይፋዊ የፖስታ መልእክት፣ በፍጆታ ክፍያ ወይም ሌላ አድራሻዎን በሚያረጋግጡ ሰነዶች ማረጋገጥ ይችላሉ። .
- **የገቢ ማረጋገጫ፥** አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢዎ በቤተሰብ አባላት ብዛት ላይ የተመሰረተውን የፕሮግራሙን ገደብ የማይበልጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርብዎታል። ይህም የ 2020 ወይም 2021 የታክስ ተመላሽ፣ የደመወዝ ክፍያ ፔይ ቼክ፣ የአሰሪዎ ደብዳቤ፣ የስራ አጥ ደብዳቤ ወይም የራስዎ ማረጋገጫ/ሰርተፍኬት ሊሆን ይችላል። በእራስዎ የሚረጋገጥ ማስረጃ ለማቅረብ የሚረዳ ቅፅ በፕሮግራሙ ድህረ-ገጽ ላይ ይገኛል። እንዲሁም በቤተሰብ አባላት ስም የተመዘገቡ የቅርብ ጊዜ የባንክ ስቴትመንቶችን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።
- **የኪራይ ማረጋገጫ።** የኪራይ ሃላፊነትዎን ፣የክፍያ ታሪክዎን እና ያለብዎትን የኪራይ መጠን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ይኖርብዎታል። ይህም በኪራይ መዝገብ፣ በሊዝ ወይም ከሌሎች ሰነዶች ጋር በመሆን አስፈላጊውን መረጃ የሚሰጥ ነው።
- የአከራይ **ሰነድ፣** አከራዩ በካውንቲው የአገልግሎት የአቅራቢዎች ምዝገባ ስርዓት እንዲመዘገብ እና የተከራይ እና አከራይ መረጃን የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲያቀርብ፣ ወርሃዊ የቤት ኪራይ መጠን እና ምን ያህል የኪራይ ገንዘብ እንዳልተከፈላቸው የሚያሳይ መረጃ እንዲያቀርብ ይጠየቃል።

**ከአሰሪ ደብዳቤ የለኝም፣ ወይም በግል ተቀጣሪ ነኝ፣ ወይም መደበኛ የስራ ሰዓት የለኝም። ገቢዬን ማረጋገጫ ምን ማሳየት አለብኝ?**

በማመልከቻው ፖርታል ውስጥ የራስዎን ማረጋገጫ መግለጫ (ስቴትመንት) ማስገባት ይችላሉ። ይህም ከኮቪድ በፊት የእርስዎን የስራ/የገቢ መረጃ እና አሁን ያለዎትን የስራ/የገቢ መረጃ ማካተት አለበት። እባክዎን ለበለጠ መመሪያ የእኛን በእራስ ማረጋገጫ ቅጽ ይመልከቱ።

**ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ታክሴ ላይ ሪፖርት ማድረግ አለብኝ?**

የለብዎትም፣ አብዛኛውን ግዜ የገንዘብ ድጋፉ በቀጥታ ለንብረቱ ባለቤት ወይም ለአከራዩ ይላካል፤ የሚላከው የክራይ ክፍያ ያለብዎትን የክራይ ክፍያ ለመክፈል ይውላል። አከራዮች የኪራይ ገቢን እንደ ኪራይ ክፍያ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

**ገንዘብ እንደደረሰኝ እንዴት አውቃለሁ?**

የጉዳይ ሰራተኛ (Social Worker) ማመልከቻዎን መገምገም ሲጀምር በስልክ፣ በኢሜል እና/ወይም በደብዳቤ ያገኝዎታል። ጉዳይዎ ለገንዘብ ድጋፍ ተቀባይነት ካገኘ፣ የጉዳይ ሰራተኛው ጉዳይዎ ያለበትን ሁኔታ ይለውጣል፣ ይህም ወደ ማመልከቻዎ ውስጥ ሲገቡ (log in) ሊያዩት ይችላሉ። ብዙ ጊዜ ገንዘቡ በቀጥታ ለአከራዩ ይላካል። የጸደቀውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የመጨረሻ ደብዳቤ ለእርስዎ እና ለአከራዩ በፖስታ ይላካል።

**ይህን ገንዘብ መልሼ መክፈል አለብኝ?**

የለብዎትም፤ ይህ ብድር አይደለም። ለካውንቲው መልሰው መክፈል የለብዎትም

**አከራዬ ኪራዬን ሙሉ በሙሉ መክፈል ካልቻልኩ ወዲያውኑ መልቀቅ እንዳለብኝ ነገረኝ። የት  መሄድ እችላለሁ?**

እርስዎን ማስወጣት የሚችለው የፍርድ ቤት ትእዛዝ ያለው ሸሪፍ ብቻ ነው። ባለንብረቱ/አከራዩ በህገ ወጥ መንገድ ሊያስወጣዎት እየሞከረ ነው ብለው ካመኑ እባክዎን የሞንትጎመሪ ካውንቲ አከራይ እና ተከራይ ጉዳዮችን በ 240-777-0311 ይደውሉ እና የፖሊስ ዲፓርትመንት የአደጋ ጊዜ ያልሆነ መስመር በ 301-279-8000 ይደውሉ። ተጨማሪ መረጃ በኮቪድ -19 የቤቶች እና የማህበረሰብ ጉዳዮች መምሪያ ( DHCA ) ላይ ይገኛል ።

**ከቤት ለማስወጣት፤ ችሎት ለመቅረብ የፍርድ ቤት መጥሪያ አለኝ፣ ምን ማድረግ አለብኝ?**

እባኮትን በአካል ችሎት ተገኝተው ለኮቪድ ኪራይ ድጋፍ ማመልከቻ እንዳመለከቱ ለዳኛው መንገርዎን ያረጋግጡ። እንዲሁም በቤቶች እና ማህበረሰብ ጉዳዮች መምሪያ ( DHCA) ኮቪድ-19 ድህረ -ገጽ ላይ ያለውን መረጃ መመልከት ይችላሉ። ።

**በኮቪድ ተፅእኖ መግለጫዬ ላይ ምን መጻፍ አለብኝ?**
ይህ ቤተሰብዎ ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ እንዴት የገንዘብ ችግር እንዳጋጠመው ግልጽ መግለጫ መሆን አለበት። ወረርሽኙ በተከሰተበት ወቅት ከፍተኛ ወጪ ወይም ሌላ የገንዘብ ችግር ካጋጠመዎት እባክዎን የቤተሰብዎን የገቢ ኪሳራ ይግለጹ። የገቢ ሰነዶችን ማቅረብ ካልቻሉ የቅድመ ወረርሽኙ ገቢዎን እና የአሁኑን ገቢዎን ማካተትዎን ያረጋግጡ ።

**ማመልከቻዎን ከማስገባቴ በፊት ሰነዶችን ማያያዝ ረስቻለሁ። ማሻሻያ ማድረግ እችላለሁ?**
አይቻልም፣ ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ ምንም ለውጥ ማድረግ አይችሉም። ከመኖርያዎ የመባረር ሁኔታዎ ካልተቀየረ ወይም የግል መረጃዎ ላይ ለውጥ ለማድረግ ካልፈለጉ በስተቀር የጉዳይ ሰራተኛ( Social Worker) እስኪያነጋግርዎት ድረስ መጠበቅ ጥሩ ነው። ሁኔታዎ ከተለወጠ ወይም የግል መረጃዎን ለውጥ ለማድረግ ከፈለጉ፣ እባክዎን የተቀየረውን መረጃ በሚከተለው የኢሜል አድራሻ ይላኩ፤ hss@montgomerycountymd.gov

**ማመልከቻዬን ካስገባሁ በኋላ ኪራይ መክፈል ያለብኝን ተጨማሪ ወራት ኪራይ መጨመር እችላለሁ?**
አይቻልም ፣ ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ መቀየር አይችሉም። ነገር ግን የጉዳይ ሰራተኛዎ (Social Worker) ማመልከቻዎን ሲገመግም የተለወጠ መረጃ ካለ ሊሰጡ ይችላሉ።

**የመገልገያ ፍጆታ ለመክፈል ድጋፍ እፈልጋለሁ። እገዛ ታደርጋላችሁ?**
አዎ፣ ለኮቪድ ኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም ብቁ ከሆኑ ለመገልገያ ፍጆታ እዳዎች እስከ 2,000 ዶላር የሚደርስ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ። ነገር ግን፣ እርስዎ የሚያገኙት ድጋፍ ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢዎ፣ የመገልገያ ፍጆታ ቀሪ እዳ እና እርስዎ ብቁ የሆኑበት የድጋፍ ወራት ብዛት ላይ የተመሰረተ ነው። እንዲሁም መስፈርቶቻቸውን ካሟሉ ለፍጆታ እርዳታ በእኛ [የቤት ኢነርጂ ቢሮ ፕሮግራሞች] በኩል እንዲያመለክቱ እናበረታታዎታለን።

**ቤት መቀየር አለብኝ ግን አቅም የለኝም። እገዛ ታደርጋላችሁ?**
የ CRRP የገንዘብ ድጋፍ የፕሮግራም የብቃት መስፈርቶችን ይሚያምዋሉ ከሆነ ለሴኩሪቲ ዲፖዚት እና እስከ ሶስት ወር የቤት ኪራይ ለመክፈል መጠቀም ይቻላል። አስቀድመው ለCRRP የገንዘብ ድጋፍ አመልክተው ከሆነ፣ እባክዎን የመኖሪያ ለውጥ ከጉዳይ ሰራተኛዎ (Case Worker) ጋር ያስተባብሩ።

ለCRRP ፈንድ ብቁ ካልሆኑ፣ ለማጓጓዣ እና የእቃ ማስቀመጫ መጋዘን ወጭዎች፣ ለደህንነት ማስያዣ እና ለመጀመሪያ ወር ኪራይ የገንዘብ ድጋፍ ልንሰጥ እንችላለን። ይህ ከኮቪድ ጋር ያልተገናኘ አካባቢ/አድራሻ የመቀየር ፍላጎት ወይም አፋጣኝ ምክንያት ከሆነ ወደ 311 ይደውሉ እና የሴኩሪቲ ዲፖዚት/ለማጓጓዝ እርዳታ ይጠይቁ።

**የጉዳይ ማለሙያ (Case Worker) ሊያገኘኝ ሞክሯል። ምላሽ መስጠት አለብኝ?**
አዎ፣ እባክዎን በተቻለዎት ፍጥነት ለጉዳይ ሰራተኛዎ ምላሽ ይስጡ። ምላሽ ካልሰጡ፣ ማመልከቻዎ ውድቅ ሊደረግ ይችላል። የጉዳይ ሰራተኞች ማመልከቻዎችን በተቻለ ፍጥነት ማከናዎን ይፈልጋሉ፣ ስለዚህ ከእነሱ ጋር መገናኘት ማመልከቻዎ ላይ ቶሎ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይረዳል። ጉዳይዎን ኬዝ ወርከር (case worker) ከያዘው ፣ በምን መልኩ እንዲያገኝዎት ባሳወቁት መሰረት የኢሜል ወይም የስልክ ግንኙነት ይጠብቁ።

**አከራዬ ለማመልከት ሊያግዘኝ ይፈልጋል። ምን ሊያደርግ ይችላል?**
አከራይዎ ሰነዶችዎን በመሰብሰብ፣ ስካን በማረግ እና ማመልከቻውን በማጠናቀቅ ሊረዳዎት ይችላል። አከራይዎ የእርስዎን ጉዳይ በመደገፍ የራሳቸውን ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ይህን የኛን ድህረ-ገጽ በመጠቀም ማመልከት ይቻላል። (mc311.com/rentrelief)

**አከራይ ተከራዩ የማመልከቻውን ክፍል ለመሙላት ፍቃደኛ ሳይሆን ወይም ተከራይ አስቀድሞ ለቆ ከወጣ ቡኋላ የእርዳታ ገንዘብ ማግኘት ይችላል?**
አይቻልም አከራይ ባይሳተፍም ማመልከቻዎችን ማስተናገድ ብንችልም፣ እርዳታ ለመስጠት ከተከራይ ደጋፊ ሰነዶችን መቀበል አለብን። በተጨማሪም፣ ተከራዩ በድጋፉ ወቅት በቦታው/አድራሻው እየኖሩ መሆን አለባቸው።

**ወደ ማመልከቻዬ እንዴት እገባለሁ?**
ማመልከቻዎን [በሚከተለው የመነሻ ገፃችን ላይ የመልከቱ www.mc311.com/rentrelief]

**ድህረ-ገጹ በትክክል አየሰራ አይደለም፣ ምን ላድርግ?**

ኢንተርኔት ኤክስፕሎረር ( Internet Explorer) ሳይሆን ጎግል ክሮምን (Google Chrome) እየተጠቀሙ መሆንዎን ያረጋግጡ ። እንዲሁም ፋየርፎክስን (Firefox) ወይም ማይክሮሶፍትን( Microsoft) መጠቀም ይችላሉ።

***ይህ መረጃ ለመጨረሻ ጊዜ የተከለሰው በኤፕሪል 28፣ 2022 ነበር።**